ፕሬስ ሪሊዝ
ጥር 10 ቀን 2000 ዓ.ም
ማስታወቂያ ሚኒስቴር

# የምርጫ ተሳትፎ የዲሞክራሲ መሰረትና የሕዝብ ሥልጣን ማረጋገጫ ነው

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የዜጎች የዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ዋነኛ ማረጋገጫ ለሆነውና በመጪው ሚያዚያ ወር 2000 ዓ.ም በመላ ኢትዮጵያ ለሚካሄደው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ የመራጮች ምዝገባ እስከ ጥር 17 ቀን 2000 ዓ.ም ይካሄዳል፡፡ እስካሁን ከመላ ሀገሪቱ በተሰባሰበ መረጃ መሰረት 15 ሚሊየን ያህል ሕዝብ በመራጭነት መመዝገቡ ታውቋል፡፡ መምረጥም ሆነ መመረጥ የዜጎች ዲሞክራሲያዊ መብትና ኩራት ከመሆኑም በተጨማሪ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ዋነኛው መሰረት መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በየደረጃው ያሉ የፌዴራልና የክልል መስተዳደር አካላት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማኅበራትና አባላት መራጩ ሕዝብ ያገለግሎኛል ብሎ እምነት የሚጥልባቸውን አመዛዝኖ እንዲመርጥ በመቀስቀስና በማስተማር ሰፊ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የተጀመረውን የሠላም፣ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በማፋጠን የኢትዮጵያን ህዳሴ የማረጋገጡ ተግባር በዋናነት ከዜጎች ውጪ በማንም እውን ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ሕዝቡ በነቂስ በመውጣት ሰርተው የሚያሰሩትን፣ ብቃትና ዝግጁነት ያላቸውን እንዲሁም ሕዝባዊ ሀላፊነት የሚሰማቸውን ተወካዮቹን ለመመረጥ ያመቸው ዘንድ በቀሩት ጥቂት ቀናት ውስጥ የመራጭነት ካርዱን በእጁ የማስገባት የዜግነት ሀላፊነትም ግዴታም ይኖርበታል፡፡ ልማትና ብልፅግናን አስቦና አልሞ ከዲሞክራሲያዊ ሂደቶች ተሳትፎ ውጪ በመሆን የሚመጣ እድገት ሊታሰብ አይችልም፡፡

የምርጫ ቦርድም የሚጠበቅበትን ሀላፊነት በተገቢው ለመወጣት በሚያስችለው አቅጣጫ በመንቀሳቀስ ምርጫው በሕጉ መሰረት ነፃና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ጥረቱን ቀጥሏል፡፡ በዚህም መሠረት ለምርጫ የሚያስፈልጉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ለምርጫው ተፈጻሚነት የሚያገለግል የጊዜ ሠሌዳ በይፋ በማውጣት ይኸው ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለውድድር የሚያበቃውን ሕጋዊ መስፈርት ያሟሉ 37 ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የመወዳደሪያ ምልክቶቻቸውን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በወጣው የምርጫ ማስፈጸሚያ መርሃ ግብር መሠረት በቀጣይ ከምርጫው ጋር የተያያዙ ቀሪ ተግባራት ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

በመሆኑም ወቅቱ ለሀገራችን ዕድገት እጅ ለእጅ ተያይዘን የምንሰራበት በመሆኑ ሕዝቡ ለመራጭነት እንዲመዘገብ በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ የቀበሌና የወረዳ መስተዳደር አካላት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሴቶች፣ የወጣቶች እና የሲቪክ ማኅበራት እስካሁን እያደረጉት ያለውን ቅስቀሳና ተሳትፎ በይበልጥ አጠናክረው በመቀጠል እየተደረገ ያለውን ጥረት በባለቤትነት ስሜት ማገዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኅብረተሰቡም ይህንኑ ተገንዝቦ ለምዝገባ በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ራሱን በማዘጋጀትና በመመዝገብ ዴሞክራሲያዊ መብቱን በተግባር ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

***በመራጭነትና በተመራጭነት መሳተፍ የዜጎች ሁሉ ብሔራዊ መብትና የዜግነት አንዱ መገለጫ ነው!!***

\#　　　#　　　#

\#